በ1918 ዓ.ም ላይ በዘመኑ ታሪክ በአደገኛነቱ አንደኛ የሆነ በጣም መጥፎ በሽታ አለምን ወሮ ነበር። በሽታው ኢንፍሉወንዛ ቢሆንም፡

የተለመደ ዓይነት ጉንፋን አልነበረም።

እንዲሁም በዚህ እትም፥
በአሁኑ ጊዜ ሊከሰት ይችላል ተብሎ ለሚፈራው የተላላፊ በሽታ ራስዎን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚችሉ ይገልጻል

NO ORDINARY FLU
እማየ፡
ይሄ ማን ነው?
FAMILY PHOTOS
ይህ ታላቁ አጎትህ አርትሮ ነው።
በስፓኒሽ ተላላፊ ኢንፍሉወንዛ ነው የሞተው—
የሴት አያታችን ማርያ ልብዋን እስኪሰበር አዝናለች ይባላል።
ገና ወጣት ነው የሚመስለው።
ምን አገኘው?

በ1918 ዓ.ም ላይ፡ የመጀመርያ የዓለም ጦርነት ወደ ማለቁ ገደማ ነበር...

ለኛ ቤተሰቦች ሁሉም ነገር ጥሩ እየሄደላቸው ነበር።

አርተሮን የማይወድ ሰው አልነበረም።

ነገር ግን ህይወት በድንገት ወደመቀየር ላይ ነው።

ከጥቂት ሳምንት በኃላ ኢንፍሉወንዛው ወደኛ መጣ እና፡ መጀመርያ የታመመችው ሰው የሴት ቅድመ አያትህ ነበረች።

ትቃጣለች። እኔ አስታምማታለሁኝ። አርተሮ ደግሞ እዛ ሱቅ ውስጥ ትሰራለህ።

በአንድ ለሊት ውስጥ፡ ህይወታቸው ተቀየረ።

እናቱ ከታመመች በኃላ፡ አርተሮ እናቱና ማርያን ያስታምም ነበር።

አርተሮ፡ ምንም ነርስ የሚባል የለንም። ብዙ ሐኪሞች እና ነርሶች ታመው ተኝተዋል። በዛ ላይ ደግሞ ብዙ የታመሙ ሰዎች ነው ያሉት።

ሱቁ ውስጥም ከዚህ የማይሻል ሁኔታ ነበር።

ይቅርታ ያድርጉልኝ የእኔ እመቤት። ከውጭ የሚመጡ እቃዎች ስለሌሉ እኮ ነው።

ከተማው በሙሉ ችግር ላይ ወደቀ።
GOING OUT OF BUSINESS
አገልግሎቶች ተሰርዘዋል
እንደ ዕድል ሆኖ፡ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ማርያ እና እናትዋ መዳን ጀመሩ።
ነገር ግን ይህ በተሰብ ገና ከችግሩ አልተላቀቀም።
ሳል! ሳል!
አርተሮ በድንገት ታመመ።
DAILY NEWS
ሳል! ሳል! ሳል!

ልክ እንደ ሌሎች ብዙ ወጣቶች፡ አርተሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ በጠና ታመመ።
በሚቀጥለው
ቀን ደግሞ ሞተ።
ለሁሉም ሰው በጣም ከባድ ጊዜ ነበር።
በጣም አዝናለሁኝ የእኔ እመቤት። የሬሳ ሳጥን አልቆብናል።
ሰዎች የኢንፍሉወንዛ በሽታ ከአንድ ወደ አንድ እያስተላለፉ ስለሆነ፡ የቀብር ስነስርዓት ወይም ሌላ ዓይነት ስብሰባ ማድረግ አንችልም።
ማርያ ከሁሉም በላይ በጣም አዘነች።
በጣም ብዙ ሰዎች ሞቱ። በዚህ ተላላፊ በሽታ ምክንያት በዓለም ውስጥ 50 ሚሊዮን ሰዎች በአሜሪካ ደግሞ 675,000 ሰዎች ሞተዋል።
በጣም ብዙ ቁጥር ነው፡ ነገር ግን አብዛኞቹ ሰዎች ደግሞ ተርፈዋል።
ማርያ—የሴት ቅድመ አያትህ--ከተረፉ ሰዎች አንድ ነች።


“ሁላችን በ1918 ዓ.ም ከነበረው ተላላፊ በሽታ የተረፉ ሰዎች የተወለድን ነን።”
ነገር ግን፡ የተላላፊው ኢንፍሉወንዛ በሽታ አደገኛነቱ እስከ አሁን አለ።
በኃላ፥
“...የጤና ተመራማሪዎች፡ አዲስ የኢንፍሉወንዛ ቫይረስ ተላላፊ በሽታ ሊያመጣ ይችላል በማለት መስጋታቸውን ገልጸዋል...”
እማየ!
FLU
“የተላላፊው ኢንፍሉወንዛ፡ ሁል ጊዜ ክረምት ላይ ከምናየው ኢንፍሉወንዛ የተለየ ነው።
FLU
የሰው አካላት ከአሁን በፊት ያላወቀው አዲስ በሆነ ቫይረስ ይነሳል።
FLU

ሰውነታችን አዲሱ ቫይረስን ለመቋቋም፡ ያስቸግረዋል።



ይህ የኢንፍሉወንዛ ቫይረስ ሲሆን፡ አንድ ሺ እጅ ጎልቶ ሲታይ ነው።

በየክረምቱ የምናየው ኢንፍሉወንዛ ሳይሆን፡ በዚህ ጊዜ ለተላላፊ ኢንፍሉወንዛ የሚሆን ክትባት የለም።

ተላላፊው ቫይረስ፡ ሰዎች ሲነካኩ ወድያውኑ የሚተላለፍ ነው።



ተላላፊው ኢንፍሉወንዛ ወደ ሁሉም የዓለም ክፍል ሊተላለፍ የሚችል ነው። በየትኛውም ቦታ፡ በይህወት ላይ ለውጥ ያመጣል።



በሽታው በፍጥነት እንዳይተላለፍ ለመከላከል፡ ትምህርት ቤቶችና መዋእለ ህጻናቶች ሊዘጉ ይችላሉ።

ብዙ ሰዎች ከስራ ይቀራሉ።





በህዝብ የሚደረጉ ዝግጅቶች
ሊቀሩ ይችላሉ።



የህክምና እንክብካቤ
ለማግኘት ያስቸግራል።

ዶክተር ቫን ደግሞ ታመዋል።
እንዴት መቀጠል እንደምንችል
አላውቅም።

ነገር ግን አብዛኞቹ የኢንፍሉዌንዛ በሽተኞች
ከእቤት ለመንከባከብ ይቻላል።

እንደ 1918 ዓይነት መጥፎ ላይሆን
ይችላል። ሁለት በጣም ከባድ ያልሆኑ
የኢንፍሉዌንዛ ተላላፊ በሽታዎች በ1957
እና 1968 ተከስተዋል።



ከባድ ባይሆኑም፡
መዘጋጀት ግን ይገባናል።

ቢያንስ ለአንድ ሳምንት* እቤት ለመቆየት መዘጋጀት አለብዎት።

* ይህ ጊዜ ቢያንስ ነው፡ ምክንያቱም ተላላፊ በሽታው ከሳምንት እስከ ወር ሊቆይ ስለሚችል።

የጤና እና የክህምና መድሃኒቶችን ማስቀመጥ ይኖርብዎታል።

ትምህርት ቤት ከተዘጋ ልጆቹን ማን እንደሚንከባከብ መወሰን አለብዎት።

ከተቻለ ከቤት ሆነው እንዴት መስራት እንደሚችሉ ፕላን ማውጣት ጥሩ ነው።

በተላላፊው በሽታ ጊዜ ጎረቤቶችዎን እንዲረዱ ይዘጋጁ።

የኢንፍሉወንዛ ጀርሞችን ይከላከሉ። ሰዎች በሚስሉና በሚያስነጥሱ ጊዜ ይተላለፋሉ።

ወይም ደግሞ፡ ጀርም ያላቸው እጆች

ጀርሞቹን ወደ ሌላ እቃ ሲያስተላልፉ።

የኢንፍሉዌንዛ ጀርም በነዚህ እቃዎች ለተወሰነ ቀን ሊቆዩ ይችላሉ።

እጆችዎን አዘውትሮው መታጠብ፡ የበለጠ መከላከያ መንገድ ነው።

ሳሙና እና ውኃ ከሌለ የእጅ ሳኒታይዘር ይጠቀሙ።

ሲስሉ እና ሲያስነጥሱ፡ በመሸፍን የኢንፍሉዌንዛ ጀርሞችን ይከላከሉ።

የኢንፍሉዌንዛ ተላላፊ በሽታ በተመለከተ ከጤና ክፍል ወይም ደግሞ ከዚህ ዌብሳይት ይማሩ።

የተላላፊ በሽታው መቼ እንደሚመጣ ማንም አያውቅም፡ አይደል?

ትክክል። ነገር ግን አሁን ከተዘጋጀን፡ ከመጣ በኃላ ብዙ ሊረዳን ይችላል።

ከባድ የኢንፍሉዌንዛ ተላላፊ በሽታ ቢሆንም ልክ እንደ ቅድመ አያትህ ማርያ፡ ብዙ ሰዎች ይድናሉ።

የቃላት መግለጫ፥

ኢንፍሉወንዛ (ወይም ጉንፋን)፥ በኢንፍሉወንዛ ቫይረስ የሚመጣ አፍንጫን፣ ጎሮሮ፣ እንዲሁም ሳምባን የሚነካ በሽታ። ጉንፋኑ ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፍ ይችላል።

ተላላፊ፥ በአንድ ቦታ ጀምሮ ወደ መላው ዓለም የሚተላልፍ በሽታ።

ቫይረስ፥ እንደ ጉንፋን፣ ወይም ደግሞ ሌሎች ከባድ በሽታች ሊያመጣ የሚችል ጀርም። ለቫይረስ አንቲባዮቲክስ መውሰድ አይጠቅምም።

ማሳሰብያዎች

በ Public Health – Seattle & King County Advanced Practice Center የተዘጋጀ

ሀሳቡ እና ታሪኩ በሜሬዲዝ ሊ-ቮልመር እና ማቲው ፍረንች የተዘጋጀ

አርትዎርክ በዴቪድ ላስክይ

የገንዘብ ድጎማ የተሰጠው በ፥ Cooperative Agreement Number U50/CCU302718 ከ Centers for Disease Control and Prevention (CDC) እስከ National Association of County & City Health Officials (NACCHO)። የዚህ ጽሑፍ ይዞታ ሙሉበሙሉ የአዘጋጆቹ ሀላፊነት ሲሆን፥ የCDC ወይም የNACCHO ሀሳብ ላይገልጽ ይችላል።